# እየሸሹ ጀግና

እንደ ትላንትናው ፣ እንዳበቀላቸው
የወንበዴ ዘመን ፣ የጫካው ኑሯቸው
ቅማልና እከኩ ፣ ያልረገፈላቸው
ከገላቸው አልፎ ፣ ዘልቆ ካንጎላቸው
በቁም የበከቱ ፣ ያበሰበሳቸው
ሲፎክቱ ያድራሉ ፣ ካንሰር ሆኖባቸው ።

ህውሃት የሚባል ፣ ተምች ባገር ገብቶ
በህልሙም በውኑም ፣ ያልታሰበ አግኝቶ
በመንደር ፣ በጎጥ ልጅ ፣ በዘር ተደራጅቶ
አጥንቷን ቆርጥሞ ፣ ስጋዋንም በልቶ
የአጋሰስ መንጋ ፣ ያገሳል ተኝቶ
እርቃኗን አስቀራት ፣ ኢትዮጵያን አራቁቶ ።

የመግደል የመዝረፍ ፣ የስርቆት በሽታ
እየመዘበሩ ፣ ባገር ሃብት ፣ ጨዋታ
የተበከለ አንጎል ፣ የማያውቅ ይሉኝታ
በሰዎች መከራ ፣ ሰቆቃና ዋይታ
ሽምቶ የሚያድር ፣ ሳቅና ጨዋታ ።

ቆም ብሎ ፣ ማሰብ ፣ የማይችል ላንዳፍታ
ልብ እንኳ እማይገዛ ፣ የማታ የማታ
ከጨዋታ ወጥቶ ፣ ከስሮ እየተረታ
ቋንጃውን ተሰብሮ ፣ ሰርኑ እየተመታ
አመሉ ሆነና ፣ በባዶ ድንፋታ ።

ከውልደት ጀምሮ ፣ ልቡ የጠለሸ
ዜጋን የቀጠፈ ፣ አገር ያበላሸ
ጥፍር የነቀለ ፣ ሰውን ያኮላሸ
ለመዝረፍ ለመግደል ፣ ቀኑ ስለመሸ
የታሪክ አተላው ፣ በደም የቆሸሸ
ሰባራ ወገቡን ፣ ቀፈቱን እያሸ
ጨርቄን ፣ ማቄን ሳይል ፣ መቀሌ ላይ ሸሸ ።

ሁሌም ዝቅተኛ ፣ በራሱ እማይኮራ
ትንሹን ትልቁን ፣ ሁሉን የሚፈራ
ጥላውን የሚሸሽ ፣ ዘላለም ደንባራ
በራሱ አይመካ ፣ እይታው ሸውራራ
መቀሌ መሽጎ ፣ ሰማነው ሲያቅራራ ።

እድሜ የተጫነው ፣ ጎባጣና አንካሳ
ማየት የተሳነው ፣ ዳፍንታም ጨንባሳ
ከዘራ ደግፎት ፣ መሄዱን የረሳ
እየሸሹ ጀግና ፣ የማጀት አንበሳ
የሙት ባልንጀራ ፣ የቆመ እሬሳ
አገር ያከረፋል ፣ ቅርናት እያገሳ
ጡረተኛ ሁሉ ፣ በሞት የተረሳ ።

ታዛቢው

December 14, 2018